# የመጨረሻው አቸናፊ፤ ኢትዮጵያዊ ራዕይና ዓላማ ያለው ብቻ ይሆናል !

የፍኖተ ዴሞክራሲ

ሐተታ ቁጥር 7

ነሐሴ 2006 ዓም

ኢትዮጵያን እንደ ሀገራቸው፤ ዜጎቿንም እንደ ሕዝባቸው አድርገው አምነው ለነጻነትና ክብር የሚታገሉ ኀይሎች፤ ማንነታቸው ወርደ-ሰፊ፤ ዜግነታቸው ምልዑ፤ ራዕያቸው ሩቅ የሆነ ዜጎች ናቸው። ሰብዕናቸውና ያለፈ ታሪካቸው፤ እንዲሁም፤ የወቅቱ ኑሯቸውና መጻኢ ዕድላቸው በሙሉ በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ የሚሽከረከር በመሆኑ፤ ኢትዮጵያዊነታቸው ያለተሸራረፈ ለመሆኑ ማንም አይጠራጠርም ። ዓላማቸው፤ ለችግር ያልተበገረ፤ ለጥቅም ያልተደራደረ መሆኑን በመራራ ትግል አስመስክረዋል። በጊዚያዊ ጸገም የማይረበሹና፤ ሁኔታዎች ዙሪያው-ገደል መስለው በሚታዩበት ወቅትም ቢሆን፤ ጨለምተኝነት የማይጠጋቸውና ተስፋ መቁረጥ የማይሞክራቸው ስለሆኑ፤ አይበገሬነታቸውን አረጋግጠዋል። የሀገራቸው ጠላቶች የሚፈሯቸውና የሚጠሏቸውም በዚሁ ማንነታቸው እንደሆነ፤ ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው። ይኸም ዕውነታ ፤ ሀገሪቱ በችግር ውስጥ በምትገባበት ጊዜ ሁሉ፤ ከመከራዋ የሚታደጉላት ልጆች የማታጣ መሆኑን ይመስክራል።

በረዥም ዘመን ታሪኳ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ የቁርጥ ቅን ልጆች አጥታ አታውቅም። ዛሬም ቢሆን ፤ ማንነታቸውን በተግባር ለመግለጽ በየቦታው አድፍጠው የሚጠባበቁና የሚታገሉ ጀግኖች እንዳሏት ተስፋ የቆረጠው ዜጋ ሁሉ ሳይቀር ጓጉቶ የሚጠባበቀው ጉዳይ ሆኗል። በብዥታ ባኅር የሚዋኘውና በትግሉ መራዘም ምክንያት ወደ ተስፋ መቁረጡ ያዘነበለው እንኳ ሳይቀር፤ ኢትዮጵያን የሚያድኑ የቁርጥ ቀን ልጆች እንዳሉ ያምናል ።

ያም ሆኖ ግን፤ ሁሉም ዜጋ የሚትከነከንበትና የሚብሰለሰልበት አንድ ቆርቋሪ ጉዳይ አለው ። ዕንቅልፍም የሚነሳው አሳሳቢ ቸግር አለው። ይኸውም፤ ኢትዮጵያዊ / ብሄራዊ ራዕይ ያለው ኀይል አለመሰባሰቡና አለመጠናከሩ ነው። ይኸ ኀይል ተጠራቅሞ ከተጠናከረ ግን ትግሉ ፤ የመጨረሻው አቸናፊ እንደሚሆን የታወቀ መሆኑንም ያምናል። **በአሁኑ ወቅት፤ በሕዝቡና በታጋዩ ኀይል መካከል^ በመተማመን ላይ የተመሰረተ መረዳዳት ሊመጣ የሚችለው ፤ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ጥቅም አንግቦ የተነሳው ታጋይ ኀይል ነጥሮ በመውጣት፤ ማንነቱን በተግባር ሲገልጽ ብቻ ይሆናል ።** ይህ ጉዳይ ለድል አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ መሆኑንም ሁሉም ዜጋ ያምንበታል። ሕዝቡም፤ ታጋይ ኀይሎች ተባብረው ማየት የዘወትር ምኞቱና ተስፋው ነው።

በኢትዮጵያ ስትረተጂያዊ ጥቅም ዙሪያ የተሰባሰበውን የአንድነት ኀይል መኖሩን የሚቃሙ ክፍሎች ፤ የነገዋን ኢትዮጵያ ትንሣኤ ማየት የማይፈልጉ ከፋፋይ ቡድኖች ብቻ ናቸው ። በመሆኑም ፤ የኅብረት ትግሉ ጥረት **" ያበቃለት የሞኝ ለቅሶ ነው"** ብለው ራሳቸውን የሚያታልሉ ጸረ አንድነት አጀንዳ የሚያራምዱ መሆናቸው አያስገርምም። የሚያስደንቀው ግን ፤እስካሁን እነርሱን ሊቋቋም የቻለ የአንድነት ኀይል ተጠናክሮ አለመውጣቱ ነው። በዚህ ምክንያት፤ የዘረኝነት አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ክፍሎችና አንቅሳቃሻቸው ወያኔ፤ ሰኔና ሰኞ ስለተገጣጠመላቸው የሀገሪቱን የፖለቲካ ምኅዳር በብቸኝነት ተቆጣጥረውታል ።

እነኝህ ጸረ ኢትዮጵያ ክፍሎች ፤ የመርኅና የአስተሳሰብ ቀውስ የገጠማቸው መሆኑን ግን አልተረዱትም። የወያኔ ዓላማና ጉዞ፤ እንኳንስ ለደጋፊዎቹና ለአጫፋሪዎቹ ቀርቶ፤ በአሁኑ ወቅት፤ የወያኔን ድርጅት ለመሰረቱትም ለራሳቸው ለዎያኔዎቹም ቢሆን ግራ አጋብቷቸዋል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ፤ ኢትዮጵያዊነት፤ በሀገራችን የፖለቲካ መልከዐ-ምድርና በዜጎቿ የአመለካከት አድማስ፤ እየጎላና እየተንሰራፋ መምጣቱ ነው ። በተለየም ደግሞ ፤ የኢትዮጵያዊነት አመለካከትና ዕምነት በአዲሱ ወጣት ትውልድ ዘንድ፤ እየሰረጸ፤ እየለመለመና እየፋፋ መምጣት፤ የዘረኝነትን አጀንዳ

ለሚያራምዱ ከፋፋይ ኀይሎች መርዶ ሆነባቸዋል። በዕርግጥም፤ ትላንትም ሆነ ዛሬ፤ ኢትዮጵያዊነትን የሚፈታተነው ኀይል አልተሳካለትም። ወደ ፊትም የሚሳካለት አይሆንም።

ዎያኔዎቹና አጫፋሪዎቻቸው ፤ ስህተትን በስህተት እየበወዙና እያተራመሱ መቀጠልን የአገዛዝ ስልታቸው አድርገው ይጠቀሙበታል። ፤ እየገደሉ በማዳንና እያዳኑ በመግደል ስልታቸው፤ በሥልጣን ኮረቻ ብዙ ጊዜ እንቆያለን ብለው ያስባሉ። ተቃዋሚያቸውን እየገደሉ መኖር፤ የነርሱን ህይወት የሚቀጥልላቸው ይመስላቸዋል ። ተቀናቃኞቻቸውን እያሰሩ መፍታት፤ እየፈቱ ማሳደድ፤ እያሳደዱም መግደልና ፤ ደብዛቸውን ማጥፋት፤ የአገዛዛቸው ዕምብርት ፖሊሲ ሆኗል ። አደገኞች ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች ቅስም እየሰበሩ፤ ሰብእናቸውን እያዋረዱ፤ የአካል፤ የዕምሮና የመንፈስ ጉዳት በማሳደር ፤ በኅብረተሰቡ መካከል ተቀባይነት ይነፈጋቸዋል ብለው ይገምታሉ። ውኀዳን መሆናቸውን ስለሚረዱ የዝቅተኝነት ሰልባ ሆነዋል። ቂም - በቀል ፤ የሥርዓታቸው መለያ ሆኗቸዋል። ይህም በበኩሉ፤ ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመምራት ተመጣጣኝ አዕምሮና ችሎታ፤ ባኅርይና መግባር ሊኖራቸው አልቻሉም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመምራት፤ ርኅሩህ ልብና፤ አርቆ ተመልካችነትና ሁለንተናዊ መለካከት እንዲኖር ያስፈልጋል። ወደ ፊት፤ እንደ ደርግ ጨካኝ፤ እንደ ወያኔ ከሃዲና አገር ሻጭ መሪዎች እንዳይመጡ፤ ካሁኑ ጠንቅቆ መታገል ይገባል።

ኢትዮጵያ በረዥም ዘመን ታሪኳ፤ እንደ አሁኑ ዓይነት አስከፊና አዋራጅ ሥርዓተ-መንግሥት ኢጋጥሟት እንደማያውቅ አያሌ የታሪክና የሥነ መንግሥት ጠበብት ይስማሙበታል። ሕዝቡን ከፋፍሎ፤ አድኅይቶና አደንቁሮ መግዛት፤ የትግል ወኔውን ይግድልበታል ብለው ይመኛሉ። ግፍና በደል ሲበዛ አመጽን እንደሚያስከትል ግን አይረዱትም። ነገ፤ ዕሳተ-ገሞራ ሆኖ ለመምጣት የተዘጋጀ ዕምቅ ኀይል እንዳለ አልተረዱትም።

አንድ ዜጋ፤ በሰብዓዊነቱ ብቻ ሊጎናጸፈው የሚገባው ክብርና ነጻነት፤ ከሚኖረው የፖለቲካ ዕምነትም ይሁን አመለካከት፤ ለይቶ ካለመረዳት የሚመጣ የማስተናገድ ችግር፤ የሀገራችንን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ህይወት ደይኖትና ጨፍልቆት ይኖራል። ይህ በመሆኑ፤ የሀገራችን የዕድገት ርምጃ ከቋቱ ጠብ ሳይል ቆይቷል።

ባለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት፤ ሀገራችን ከአንድ ጽንፍ ወደ ሌላ ጽንፍ እየተላጉ በተፈራረቁ የሥርዓት ለውጦች ብታልፍም፤ የዜጎቿ የፖለቲካ ነጻነትም ይሁን የኢኮኖሚ ህይውት፤ በመሠረታዊ መልኩ አልተቀየረም። ከንጉሳዊ ፈላጭ-ቆራጭ ሥርዓት ፤ ወደ ወታደራዊ / አርመኒያዊ አምባገነን አገዛዝ፤ ቀጥሎም፤ ጊዜው ወደ አለፈበት የጎሳ ክፍፍል ዘቅዝቃ ብትወርድም፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ እየፈጩ ጥሬ ሆኖ ቀርቷል። ተፈራራቂው ሁሉ፤ **ትሻልን ሰድጀ፤ ትብስን አመጣሁ** ከመባል አላለፈም። የዚህ ችግር ዓይነተኛ ምክንያት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅምና ፍላጎት ያገናዘበ ራዕይ ዕጦት መሆኑ ለማነኛውም ዜጋ ግልጽ ነው። የሀገሪቱን ስትራተጂያዊ ጥቅም አንግቦ የሚነሳ ትግል ፤ የመጨረሻውን ድል ይጎናጸፋል የሚባለውም በዚህ አሳማኝ ምክንያት እንደሆነ፤ አርቆ አስተዋይ ዜጋ ሁሉ ይስማማበታል።

በአንጻሩ ደግሞ፤ ትግል የሚጀምረው ሁሉ የመጀመሪያ ዓላማው ፤ ሕዝብን ነጻ ለማውጣት መሆኑ ቀርቶ፤ ለሥልጣን ብቻ የሚያቋምጥ ከሆነ፤ የሕዝብንና የሀገርን መሠርታዊ ጥቅም ያስገኛል ትብሎ አይጠበቅም። የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሊለወጥ ያልቻለውም በዚህ መሠረታዊ ምክንያት ነው። ዋስትና ያለው ሙሉ ነጻነት የሚገኘውና የሚረጋገጠው፤ በሕዝብ ቀጥታ ተሳትፎ በሚደረግ ትግል መሆኑ ሁሉም ሊረዳው ይገባል።

የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ማዕከል አድርጎ የሚታገል ኀይል፤ አመለካከቱን በአልፎ ሃጅ ሥነአዕምሮ የሸበበ ባለመሆኑ፤ ለጊዚያዊ ችንፈት እንደማይረበሽ ሁሉ፤ ለአፍለኛ ድልም ቢሆን ረክቶ የሚዝናና አይደለም። " **ቢቀናኝ ገሲጋሽ፤ ቢከፋኝ ተመላሽ** " በሚል ዕሳቤ የሚንቀሳቀስ ትግል፤ አንድ መባቻ እንኳን የሚያስቆጥር ዕድሜ አይኖረውም። ለዚህም ነው፤ ለቁጥር የሚያስቸግር ብዛት የነበራቸው ድርጅቶችና ስብስቦች፤ እንደ ሰኔ እንጉዳይ እየፈሉ፤ እንደ ሐምሌ ጉም እየተነኑ የጠፉት! አንድ አንድ ክፍሎች፤ የድርጅቶችን መክሰምና የትግሉ ዳር ድምበር ካለመድረስ የመጣ ጭንቀት ምክንያት፤ ከደርጅት ላይ ሌላ ድርጅት እየፈጠሩና አዳዲሶችንም እየቀፈቀፉ፤ በትግሉ ላይ አሉታዊ ትጵዕኖ በማሳደር ላይ የሚገኙት። **ከጥራት ይልቅ፤ በብዛት ላይ ብቻ የማተኮር አባዜ፤ አጥጋቢ ውጤት ሊያስመዘግብ ቀርቶ፤ ርምጃውንም እንኳን ፈቀቅ ሊያደርገው አልቻለም።** ሙከራውና ጥረቱ ሁሉ ባለህበት ዕርገጥ ሆኖ ቀርቷል። የዝብሪት ቤት ክፍት ሆኖ ስለሚገኝና ባለቤትም በማጣቱ ምክንያት ፤ የአልፎ ሃጁ ሁሉ መጫዎቻ ሆኖ ይቀራል። ኢትዮጵያን ከገጠማት

ችግር ነጻ ለማውጣት የሚደረገው ትግል እስካሁን ድረስ የታለመለትን ግብ ሳይመታ የዘገየውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ አስተያየታቸውን በቁጭት የሚግልጹ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ በቅርብ እየተከታተሉ ያሉ ተዛቢዎች ዕምነት ሆኗል።

በመጀመሪያ ደረጃ፤ ሀገሪቱ አሁን ከገጠማት ሁለንተናዊ ችግር ነጻ ያወጧታል ተብለው የሚጠበቅባቸው፤ የፖለቲካ ኀይሎች ተጠያቂነት፤ ኃላፊነትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የምሁሩ ማኀበረሰብና ልዩ ልዩ ተቋማትም ቢሆኑ፤ ከተጠያቂነት ውጭ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም፤ ሀገሪቱ የሁሉም ዜጋ ነች እስከተባለ ድርስ፤ ለጥፋቷም ይሁን ለልምቷ ሁሉም ተጠያቂ ስለሚሆን ነው። ማነኛው ዜጋ፤ የየድርሻውን መወጣት እንደሚገባው ሌላው ሊያስገድደውና ሊያባብለው አይገባም ። ድርሻን የመውጣትና ግዴታን የመፈጸም ተልዕኮ ፤ አንዱ ከሌላው ይሻላል ተብሎ የሚሽጋሽግና የሚተካካ ተግባር አይደለም። **ትግል፤ በስማ-በለውና በቀላጤ ሊሆን አይችልም።** የሀገር ጉዳይ፤ ሌሎች ይስሩት እንጅ፤ እኛን አይመለከትም በሚል አባዜ፤ አንዱ በሌላው ላይ ጣት መጠቋቆሙ፤ ለችግሩ መፍተሄ ርባና አያመጣም። የእስካሁኑ ትዝብት እንደሚያስረዳው ከሆነ ፤ "**የፖለቲካ ድርጅቶችና ስብስቦች ምን እየሰሩ ነው ?**" የሚለው ተደጋግም ሲጠየቅ ዓመታት አልፈዋል። ይህ ጉንጭ-አልፋ ክርርክር ግን እስካሁን ያስገኘው ፋይዳ የለም።

ይህንን ሃቅ የተረዱ ጥቂት ምሁራንና ሌሎች ሀገር-ወዳድ ዜጎች ፤በትናጠልም ይሁን በቡድን እየሆኑ፤ የተቻላቸውን ጥረት እያደረጉ መሆናቸው ባይዘነጋም፤ ሁሉም የተማረው ክፍል ተባብሮ በመነሳት ያመረቅ ውጤት ሊያስመዘግብ አልተቻለውም። የምሁሩ ማኅበርሰብ ሀገርን በማዳኑ ጥረት ላይ ቀጣይነት ባለው መልኩ ቢተባበር፤ ዓይነተኛ ሚና እንደሚጫወት ማንም ሊክድ አይችልም። በተለይም ደግሞ፤ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም ማስጠበቅን ማዕከል ባደረግ ትግል ላይ አስተዋጽኦ ቢያደርግ፤ ለትግሉ ሂደት እምርታ ሊሰጥ ይችላል። ብሄራዊ ነጻነትን ለመጎናጸፍ የሚደረገው ትግል እንዲፋጠን ከተፈለገ፤ ሁሉም የአቅሙን ማደረግ እንደሚገባው አስታዋሽ የሚያስፈልገው አይደለም። የየአቅሙን ማድረግ አለበት ሲባል ፤ የአዕምሮ፤ የቆሳቁስና የነዋይ አስተዋጸኦን ሁሉ ያካትታል። የነጻነት ዋጋው እጅግ ሲበዛ ውድ በመሆኑ፤ ህይውትን ከመገበር አንስቶ እስከ ጥቃቅን ቁሳቁሳች መለገስን ሁሉ ያጠቃልላል። የፖለቲካ ድርጅቶች በትግሉ የመጀመሪያውን ረድፍ በመያዝ ግምባር ቀደሙን ሚና በመጫዎት፤ ትግሉ የሚጠይቀውን መሥዋዕት ለመክፈል የተዘጋጁ ቢሆንም፤ የነርሱ የተናጠል ተጋድሎ ብቻውን ለድል አያበቃም።

የብሄራዊ ነጻነት ትግል ግቡን የሚመታው፤ሁሉም ዜጋ፤ እየከተተ ሲመክት ብቻ ነው። የክተት- መክት አዋጅና ብሄራዊ ጥሪ ደግሞ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ነገር አይደለም። ሕዝባዊ አመጽና አምባገነን ሥርዓት እሳትና ገለባ ስለሆኑ፤ ዎያኔና ተባባሪዎቹ የሕዝባዊ አመጽን ሽውታ ሲሰሙ ብርክ እንደሚይዛቸው በሚገባ እናውቃለን። ምክንያቱም፤ የሀገሪቱን ችግር፤ በዘላቂ መልኩ ለማስውገድና የሕዝቡን ሙሉ ነጻነት ለማስገኘት የሚታገለው ኀይል፤ የመጨረሻው ድል አድራጊ መሆኑ ስለሚታወቅ ነው። ድል አድራጊ የሚሆነውም፤ የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍና ትብበር፤ ተሳትፎና ይሁንታ ስለሚያገኝ ነው።

እስካሁን ድረስ ፤ የጋራ ችንፈትን እንጅ የጋራ ድልን የማያውቀው የተቃውሚ ኀይል ፤ የዜሮ ድምር ጨዋታውን (ዜሮ ሳም ጌም) አቁሞ፤ ሁሉም አቸናፊ የሚሆንበትን ( ዊን-ዊን ) የፖለቲካ ስልት መንደፍ እንዳለበት የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ያስገድደዋል። ይህንን ሀቅ መገንዘብ፤ "**ትግል በቆረጣ** " ከሚለው ውዥምብር ነጻ ያደርጋል። ለጊዚያዊ ጥቅም እየተደለሉ፤ የጥፋት አውራ ከመሆንም ያድናል። ከእንግዲህ ወዲያ የተራዘመ አመጽ ማድረግ አይቻልም የሚለው የተነበ አመለካከት፤ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ለማጣትና ተቸናፊነትን ለመደብቅ ሲባል የሚሰነዝር ምክንያት በመሆኑ፤ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም። የሥርዓቱ አራማጆች ጠንካሮች ስለሆኑ፤ እነርሱን መቃውም የደርግን ዘመን መርሳት ይሆናል የሚለው አመክንዮ ( ሎጂክ) የዘረኛ ሥርዓት፤ በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ እንዲኖር መፍቀድ ይሆናል። ይህ ደግሞ በበኩሉ፤ ኢትዮጵያ መኖር የለባትም ብለው ከፈረዱባት ጠላቶች ጋር መተባባር ይሆናል ። በታሪክና በትውልድ የፍርድ ሸንጎ የሚያስጠይቅ ብሄራዊ ወንጀል !

የወያኔ መሪዎች ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ከጊዜ ጋር በመሻማት ላይ መሆናቸውን በመረዳት፤ በተመሳሳይ መልኩ በተቃዋሚው በኩል፤ ከጊዜ ጋር የመሽቀዳደም ሂደት ካልተደረገ፤ "**ቁጭ ብለው ጠበቁን፤ አልፈናቸው ሄድን !**" ለሚል ስላቅ ሰለባና መቀለጃ መሆን ነው ። የወያኔ መሪዎች፤ የተቃዋሚው ኀይል የኋላ ኋላ ተጠናክሮ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ስለሚረዱት፤ ከአደጋው ለመከላከል ሲሉ አስቅድመው የማያደርጉት ጥረት የለም።

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ አዲስ አበባ ላይ፤ ከሰዳኖች ጋር የደረጉት የጋራ መከላከያ ስምምነትና የጦር ኃይሎቻቸው የትብብር ሰነድ መፈራረማቸው ፤ ለዚህ አባባል እንደ ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል ። ወያኔና ሱዳኖች ለምን ይህንን ስምምነት እንደተዋዋሉ መረዳት ከባድ አይደለም። የወያኔዎቹ ዓላማ፤ ከማይቅርላቸው፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ሊከላከልላቸው የሚችል ረዳት መፈልግ ነው። ወያኔን፤ የሱዳኖች ቀርቶ የምዕራባውያን ኀይል፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቆጣ ሊያድነው አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብና ብሄራዊ ጥቅማቸውን አንግቦ የሚታገልው ኀይል የመጭረሻው አቸናፊዎች እንደሚሆኑ ማንም አይጠራጠርም ።

የጊዜ ጉዳይ ከተነሳ፤ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አመፅ ከፈነዳ ወደ ግማሽ ምዕተ-ዓመት ( 50) ሊጠጋው ነው። በዘመናት ቀመር ሲታይ አያሌ ጊዜ መሆኑ ባየካድም፤ ሕዝባዊው አመፅ ያነሳቸው መሠረታዊ የነበሩት የሕዝብ ጥያቄዎች ግን አብዛኛዎቹ እስካሁን ሳይመለሱ ቅርተዋል። ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት ሆኖ የሚወሰደው፤ የኢትዮጵያ ዐብዮት ሁነኛ ባለቤት የማጣቱ ጉዳይ ነው። ኃላፊነትና ወገንተኝነት የጎደላቸው ሁለት ተወራራሽ አምባገነን ሥርዓቶች፤ ለሕዝብ የተፈጠሩና የቆሙ ባለመሆናቸው፤ እስካሁን ጥፋትን እንጅ በጎ ተግባር አላስመዘገቡም። መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎቹም አልተመለሱም። ባንጻሩ የተደርጉት ግን ፤ ሀገሪቱን ሰው አልባ ማስቀረት፤ የተማረውን ማጥፋት፤ ወጣቱን መፍጀት፤ ታሪክን ባኀልንና ቅርስን፤ የሀገርንም ህልውና አደጋ ላይ መጣልን ነው። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት አሁን አገሪቱ ያልችበት ሁኔታ ሆኗል።

ይህንን፤ ለዝክረ- ታሪክ እና ለተተኪው ትውልድ ማስገንዘቢያ እየመዘገቡ በማለፍ፤ በሀገራችን ወቅታዊ ችግሮች ማሰውጋጃ ላይ ማተኮሩ ተገቢ መሆኑን እናምናለን። ያለፈውን ድርጊት መመዝገብ፤ ከጎሊና ወቀሳ ነጻ የሆኑ ታሪክ ዘጋቢዎች ተልዕኮ ነው ተብሎ ሲለሚታሰብ፤ ያለፈውን እያሰቡ ማውጠንጠን፤ ለአሁኑ ችግር መፍተሄ የሚያመጣው ፋይዳ አይኖረውም። በሀገራችን ችግሮች መፍተሄ ላይ ማተኮሩ ወቅታዊና አንገብጋቢ መሆኑን፤ ሁሉም ዜጋ የሚያምንበት ነው። በመፍተሄዎቹ ፍለጋ ላይ ለማተኮር፤ የሚከተሉትን **ግንዘቤዎች ዕሳቤ ውስጥ ማስገባት** የጠቅማል ተብሎም ይገመታል።

- የሀገሪቱን በሄራዊ ጥቅም የመጠበቅና የማስከበር ዓላማ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ሁሉም ማመን አለበት። ይህንን ዓላማ አንግቦ የሚታገል ኀይል፤ የመጨረሻው አቸናፊ መሆኑ የማይቀር ነውና።

- የታሰበውን ግብ ለመምታት ከተፈለገ፤ ፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚንቀሳቀሰውን ትግል መደገፍ አማረጭ አይኖረውም። በመሠረታዊ መልኩ፤ የትግሉ አጋር የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፤ ለትግሉ፤ ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር ሊያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ደግሞ፤ የሀገሪቱ ምሁራንና ተቋማት ያላተቆጠበና ያልተቋረጠ ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል። በትግሉ ሂደትም ፤ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበባቸዋል ። ይህንን ማደረግ፤ የሕዝቡን ውለታ እንደመክፈል ይቆጠራል። እያንዳንዳቸው አዛውንት ምሁራን የተማሩት፤ ደሃው ገበሬ በከፈለው ግብር መሆኑን አይዘነጉትም።

- ካለፈ የዞረ-ድምር ስሌት ተላቅቆ፤ ሀገሪቱ በገጠማት ችግር መፍተሄ ላይ ማተኮር፤ የትግሉን ዕድሜ ያሳጥረዋል ተብሎ ይታመናል። ለአለፈ ክረምት ቤት ስለማየሰራ፤ የዛሬውን ችግር እያስወገዱ በሀገሪቱ መፃዒ ዕድል ላይ ማተኮሩ ከዘላቂ መፍተሄዎቹ ማከካል የመጀመሪያው ይሆናል።

- አቸናፊና ተቸናፊ የማይኮንበት፤ በአንጻሩ ግን ሁሉም አቸናፊና ተጠቃሚ ለሚሆንበት የሚችል ሥርዓት መዘጋጀት ለዘላቂ ሠላምና ማረጋጋት፤ ለልማትና ዕድገት፤ መሠረት ይሆናል ተብሎ የታመናል። ሠላምና መረጋጋት፤ ልማትና ዕድገት ዋስትና የሚኖረው ግን፤ የሕዝብ ሙሉ ነጻነት ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ፤ በዘመነ ዎያኔ የሚሆን አይደለም። የዘርኞች ሥርዓት መወገድ ግዴታ የሚሆነውም፤ በዚህ ምክንያት ነው።

- የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ በዘርና ቋንቋ ላይ በተማከለ የፖለቲካ ማዕቀፍ ውስጥ ሊገባ እንደማይፈልግ ማረጋገጡ መታወቅ አለበት። ዘረኛና ከፋፋይ ፖለቲካ፤ ለሕዝብ አንድነትና ለሀገር ደኅንነት ጠንቅ መሆኑ ማነኛውም ዜጋ ተረድቶታል።

- የሀገራቸውን ችግር የሚፈቱት፤  ራሳቸው ኢትዮጵያውያን/ያት እንጅ የውጭ ባዕዳን እንደማይሆኑ  ያለፈው ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ ወቅታዊው-  ነባራዊ ሁኔታ አረጋግጦታል ። በመሆኑም፤በባዕዳን  የሚፍጠርና የሚደገፍ መንግሥት በሕዝብ ዘንድ ተቀባነት የለውም ። **ኢትዮጵያዊ መንግሥት ማቋቋም አልፋና ዖሜጋ ነው !**

**ኢትዮጵያ ለዘለዓም ትኖራለች !**

//////////////////////////////////////----------------------/////////////////////////////////